# ሰው ለጥያቄው መልስ የሚያገኘው ሲያምፅ ከሆነ ፥ ኑ እናምፅ

## ጌታቸው ኃይሌ

መሣሪያ አንሥተው በኢሕአዴግ ላይ ያመፁ ቡድኖች ፥ ኢሕአዴግ "ግቡ" ብሎ ጋብዟቸው አገራቸው ገብተዋል ። ስለ አመፁና "አንታዘዝም" ስላሉ ፥ ድምፃቸው ተሰማ ፤ ጥያቄያቸው ተመለሰ ። አንዳንዶቹማ ሲጋበዙ ትጥቅ እንዲፈቱ እንዳልተጠየቁ ሲናገሩ ሰምተናቸዋል ። ይህ "የአፍ ወለምታ" ሊሆን ይችል እንደሆነ ነው እንጂ ፥ "አሉ ባልታ" ወይም "ተረት ተረት" አይደለም ። ይኸው ከመንግሥቱ የጦር ሠራዊት ጋር እየተዋጉ ነው ። "ብፈልግ ኢትዮጵያን ልከፋፍላት እችላለሁ" የሚለውና ጠቅላይ ሚኒስትራችንን ሲያንጓጥጥ የኖረው ፥ ሳንጃውን በክርስቲያኑ ሕዝብ ላይ ሲመዝ በይፋ የታየውም ተጋብዞ ፥ ኢትዮጵያ ገብቶ ፥ በሸራተን ሆቴል መሽጎ ይዶልታል አሉ ። እኛ ግን ፥ "እኛ ኢትዮጵያውያን ከተለያዩ ጎሳዎች የተውጣጣን አንድ ሕዝብ ነን እንጂ ፥ ጎሰኞች አይደለንም ፤ ጎሰኞች አታድርጉን" እያልን ጉሮሯችን እስኪደርቅ ብንጮህ ፥ ብዕራችን እስኪነጥፍ ብንጽፍ ፥ ጆሮ ዳባ ልበስ ተባልን ። ለምን?

የአለመሰማት ጉዳይ የጥንት ነው ፤ "ደግን ልጅ እናቱም አትወደውም" ይባላል ። ኩበት የምታስለቅመው ፥ ጌሾ የምታስወቅጠው ፥ መንደር ለመንደር የምትልከው ፥ "እሺ እማየ" የሚለውን ልጅ ነው ። ቅዱሱ መጽሐፍም መስክሯል ። ከአባቱ ድርሻውን ወስዶ በወሮበላነት የኖረው ልጅ ተመልሶ ሲመጣ ለጨዋውና ለታማኙ ወንድሙ ያልተደረገለት ታላቅ ድግስ ተደረገለት ። ጨዋው ልጅ ፥ "መልካም ልደት" እንኳን አልተዘመረለትም ። "እነሆ ይህን ያህል ዓመት እንደባሪያህ ተገዝቼልሃለሁ ፤ ከትእዛዝህም ከቶ አልተላለፍኩም ። ለእኔም ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ ጥቦት እንኳ አልሰጠኸኝም ፤ ነገር ግን ይህ ልጅህ ገንዘብህን ከጋለሞቶች ጋር በልቶ በመጣ ጊዜ የሰባውን ፍሪዳ አረድክለት" ብሎ በአባቱ ላይ ቢያጉረመርም ፥ የተሰጠው መልስ ፥ "አንተ ሁል ጊዜ ከእኔ ጋር ነህ" የሚል ነበር ። እኛንም ፥ "እነሱ ምንም ቢያጉረመርሙ ፥ ከኢትዮጵያ አይለዩም" ተብለን የሚሰማን አላገኘንም ።

እውነት ነው ፤ ብዙዎቻችን እንኳን አለመሰማት ሥቃይም ቢሆን ከእናት ኢትዮጵያ አይለየንም ። ግን ቀስ በቀስ በበሽታው እየተለከፍን ነው ። ጥቂቶቻችን ከኢትዮጵያ ይልቅ ለነገዳችን ማሰብ ጀምረናል ። "ብሔር ፥ ብሔረሰብ" የሚባሉትን ቃላት ከአፋቸው አስገብተው የማያውቁ ሰዎች ፥ ዛሬ የፖለቲካ ንግግራቸውን የሚጀምሩት በነዚህ ቃላት ሆኗል ። በዚህ የጎሳ ፖለቲካ መግነን ምክንያት ቊጥራቸው እንዳይጨምር በሥጋት ላይ ነን ።

ጩኸታችን ያልተሰማለት ብሶታችን ጎሰኝነት ነው ። ያ አጼ በጉልበቱ ፥ የኢትዮጵያን አንድነት ከሚዋጉ ከአነጎች ጋር ሆኖ ፥ ኢትዮጵያን እየቈራረሰ ካከፋፈለን ከ1983 ዓ. ም. ጀምሮ ፥ "እኛ ኢትዮጵያውያን ጎሳችን የተለያየ ቢሆንም ፥ አንድ ሕዝብ ነን" እያልን ስንጮህ ፥ ባለሥልጣኖቻችን ከኛ ጋራ እልህ የገቡ ይመስል ፥ በአነጋገሩን ቊጥር ፥ "ብሔር ፥ ብሔረ ሰቦች ፥ ሕዝቦች" ማለታቸውን አባብሰውታል ። እኛ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆነን ሳለ ፥ ጆሯቸውን የሚሰጡት ለጠባቡ ሕዝብ ነው ። ጎሰኝነት ሲያጋድለን እያዩ ፥ ከዚያም አልፈው ፥ የመንግሥት ሥልጣን ለጎሳዎች ከማከፋፈል ችግር ውስጥ ገቡ ። የገቡት ከማጥ ውስጥ መሆኑ ሲታያቸው ፥ ሐሳባቸውን በመለወጥ ፈንታ ፥ የምናዝንላቸው ይመስል ፥ ከማጡ ለመውጣት

እንዴት እንደተቸገሩ ይነግሩናል ። የንጹሓን ክልል እንደሌለ እየታወቀ ፥ ሥርዓቱን አንዱ ሲጠላው ሌላው የሚወደው ለምን ይሆን? ሌላውን ኢትዮጵያዊ በመግደልና በማባረር ለማጽዳት ይሆን?

እንግዲህ አንሰማችሁም ካሉን ፥ አምፀው እንደተሰሙት ድርጅቶች እንድንሰማ ፥ ኑ እኛም እናምፅ ፥ ኑ እናድም ። በነዚህ ከፋፋይ መጠሪያዎች ሲጠሩን አንሰማቸው ፤ እንደ ደብረ ጽሙና መነኮሳት ፥ ዝም ፥ ጭጭ እንበል ። ወደኛ ሲያዩ ፊታችንን ወደሌላ እናዙርባቸው ። "አቤት ወይም እመት ያለ የኢትዮጵያ ጠላት ይሁን" ብለን እንግማግል ። መግሪያችን ኮርፌያ ነው ።

ውድ ጠቅላይ ሚንስትራችን በነዚህ ጆሯችንን በሚቆረቁሩ ስሞች ይጠሩንና ከዚያ ቀጥሎ ፥ በሚጥሙን ቃላት እንደ አንድ ሕዝብ ያነጋግረናል ። ምናልባት ፥ "ብሔር ፥ ብሔረሰብ ፥ ሕዝቦች" የሚለን በመሐላ የተረከበው ሕገ መንግሥት እስኪሻሻል ድረስ ማክበሩ ይሆን? ምክንያቱ እውነት ይህ ከሆነ ፥

(ሀ) ሕገ መንግሥቱ የሚሻሻልበት ቀን ወይም ሁኔታ ይነገረን ፤

(ለ) ጥያቄያችን አጀንዳ ውስጥ እንደሚገባም ይረጋገጥልን ፤

(ሐ) (1) ኢትዮጵያን የከፋፈሏት ሁለት የኢትዮጵያን አንድነት የሚጠሉ ድርጅቶች መሆናቸው ፥ (2) የተረፈውን በቅርጫ ያከፋፈሉን ለራሳቸው የፈለጉትን ያህል ወስደው መሆኑ ፥ (3) እነዚህ ወንጀለኞች ይህን ወንጀል የፈጸሙት በቅርቻጫው ጊዜ የተበደሉ እንዳይቃወሟቸው ፥ ተደብቀው መሆኑ ይታወቅልን ።

እነዚህን ጥያቄዎች አንድ ሰው ያርቅቃቸው እንጂ ፥ የብዙዎች ፥ የእጅግ ብዙዎች ጥያቄዎች መሆናቸው በየቀኑ የሚታይ ፥ የሚሰማ ፥ የሚነበብ ሐቅ ነው ። "እናንተ እነማናችሁ?" የሚለን ካለ ፥ "ዶክተር ዐቢይ ሕወሐትና ኦነግ በማህላችን የገነቡትን የከፋፋይ ድምበር ያፈርስልናል" በሚል ጽኑ እምነትና ሙሉ ተስፋ ፥ በሄደበት ቦታ ሁሉ "ዐቢይ ፥ ዐቢይ" እያልን የምንጠራው ኢትዮጵያውያን ነን ። መጠናችንን ለማወቅ ከፈለገ ፥ እኛ አኩርፈን ከቀረንበት ቦታ ይሂድና ስንት ሰው እንደሚያጅበው ይይ ። "የሕዝብ ድምፅ መሰማት አለበት ብሎ" ቈርጦ የተነሣ መሪ ይኸንን የሕዝብ ድምፅ ችላ ብሎ በሰላም መኖር አይችልም ። ደግሞም እኮ ፥ በጎሳችን መጠራት "ኋላ-ቀሮች ናችሁ" ማለት ነው ። ኢትዮጵያ ኋላ-ቀር ልጆች እንዳሏት እናውቃለን ፤ ግን እጅግ ጥቂቶች ናቸው ። ጥቂቶች ከሆኑ ፥ በዘመነ ዲሞክራሲ የብዙዎች ድምፅ በጥቂቶች ድምፅ አይጨቈንም ።

ጥያቄዎቻችን ከለውጡ አጀንዳ ውስጥ መግባታቸውን እስክንሰማ ድረስ እናምፃለን ። "ለአመፃችን መሪ ያስፈልገናል" የሚል ካለ ፥ አግኝተናል ። ክቡር አቶ ሙስጠፋ መሐመድ ዑመር ይባላል ። አዲስ የተሾመው የሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዴንት ነው ። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ ያለውን ትልቅ ኀላፊነት ትቶ ወደ ሀገሩ የተመለሰው ፥ የምንፈልገው መሪ ለመሆን ነው ። የመጣው ኢትዮጵያን ከለከፋት የጎሰኝነት በሽታ ለማላቀቅ መድኃኒት ይዞ ነው ። ተጠራጣሪዎች ካላችሁ ፥ ይህ እንደ ክቡር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና እንደ ክቡር አቶ ለማ መገርሳ ለኢትዮጵያ በጭንቋ ጊዜ የደረሰላት ልጇ ከአቶ ካሣሁን ነገዎ ጋራ ያደረገውን ቃለ ምልልስ ስሙት ፤

https://www.sbs.com.au/yourlanguage/amharic/en/audiotrack/mustafa-builder-my-somali-ethiopian-identities-are-intertwined

ጎሰኞች ፥ “መብታችን ይከበርልን” ሲሉ ይሰማሉ ። መብታቸው ተጥሶ ከሆነ ጥያቄያቸው የሚገባ ነው ። የመብት መከበር ጉዳይ የብዙዎቻችን ጨኸት ነው ። እንደ እውነቱ ከሆነ ፥ “የሌላው መብት ይጣስ” የሚሉ ጎሰኞች ብቻ ናቸው ፤ “ለኛ ተከልሎ በተሰጠን የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር የሌላ ክልል ኢትዮጵያዊ አይምጣብን” ይላሉ ። የሌላውን መብት መጣስ ማለት ይህ ነው ። ብዙዎቻችን ፥ “የዲሞክራሲ ያለህ” እያልን የምንጮኸው የዲሞክራሲ ዋና ጥቅሙ የማንንም ዜጋ መብት እኩል የሚያስከብር ስለሆነ ነው ። ዲሞክራሲን ተቀብሎ ፥ ዲሞክራሲ የሚፈቅደውን መብትና የሚጠይቀውን ግዴታ አናከብርም ማለት አይቻልም ። ጎሰኞች ግን ጎሳቸውን ለማዳበር ሙሉ ነፃነት ከመጠየቅ አልፈው ተጨማሪ መብት ይሰጠን ሲሉ ይሰማሉ ። “ከሌሎች መብት ላይ ተቀንሶ ለኛ ይጨመርልን” ማለታቸው ነው ። “አትንኩኝ ፤ ለሌላው የሚሰጥ ማናቸው ነገር ለኔ አይነፈገኝ” ከማለት በቀር ሌላ ምን የመብት ጥያቄ አለ?

ኋላ-ቀር ለመሆን ያልተማረ መሆን አያስፈልግም ። ለምሳሌ ፥ በዚህ ጉዳይ የሊቁን የፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስን አቋም እንመልከት ፤ የለንደኑ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በአዘጋጀው የምሁራን ውይይት ላይ ፥ ፕሮፌሰር በየነ ይኸንን ጥያቄ እንደኛ የሚያሣውን ሁሉ ፥ “ለስንትና ስንት ዓመታት በነሱ የፖለቲካ ቅኝት የገዙን ልጆችና የልጅ ልጆች ናቸው” አለው ። የስብሰባው አዘጋጅም ትዝብቱን አደነቀለት ። ፕሮፌሰር በየነ ፥ “አለባብሶ ቢያርሱ” የሚለውን ምሳሌ ጠቅሶ ፥ የወረፈው አማራዎቹን መሆኑን ፊት ለፊት ሳይናገር ፥ አለባብሶ አለፈው ። አላወቀውም እንጂ ፥ የወረፈው የኩርፊያችን መሪ ያደረግነውን አቶ ሙስጠፋ መሐመድ ዑመርንና አያቶቹን ጭምር ነው ። የወረፈው ዶክተር ብርሃኑ ነጋንና አያቶቹን ጭምር ነው ። የወረፈው ጎሰኝነትን የሚነቅፉ የብዙ ጎሳዎች ልጆችንና አያቶቻቸውን ጭምር ነው ።

እስቲ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስን ጠይቁልን ፤ እነዚህ ከላይ ያነሣኋቸው የተከበሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን “ለስንትና ስንት ዓመታት ገዙን” የሚላቸው ልጆችና የልጅ ልጆች ናቸው ወይስ አይደሉም? ካይደሉ ፥ እነሱ የሚሉትን ሲሰማ ፥ አማራውን ከመንቀፍ ይልቅ መሳሳቱን ቢገነዘብ አይሻልም ነበር? የአቶ ሙስጠፋ መሐመድ ዑመርን የትምህርት ደረጃ ባላውቅም ፥ የፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ትምህርት የመጠቀ ነው ። በአሳተማቸው ጥናቶች ምክንያት በዓለም ደረጃ በመከበሩ ኢትዮጵያንና አስተማሪዎቹን (እኔን ጨምሮ) አኮርቷል ። ሆኖም ፥ ማን ወደፊት ማን ወደ ኋላ እንደሚያይ ስትመለከቱ ፥ “ኋላ-ቀር ለመሆን ያልተማረ መሆን አያስፈልግም” ያልኩበትን ምክንያት ትረዱልኛላችሁ ።

ኢትዮጵያ በነፃ ለዘላለም ትኑር ። የነፃነት ጮራ ለፈነጠቁልን ለክቡር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ፥ ለክቡር አቶ ለማ መገርሳ ፥ ለክቡር አቶ ደመቀ መኰንን ፥ ለክቡር አቶ ደጉ አንዳርጋቸው ሙሉ ጤናና ረጅም እድሜ ይስጣቸው ። ከያዙት የቀና መንገድ የሚያስወጣ ደንቃራ አያጋጥማቸው ። እኛንም ዶክተር ዐቢይ በፍራንክፈርቱ ንግግሩ ላይ ለኢትዮጵያ ተስፋ ያደረገላት አንድ ባንድ ሲፈጸም ለማየት ያብቃን ። አሜን ።